homes victoria

VICTORIA State Government | Families, Fairness and Housing

Amharic | አማርኛ



ምስል፦ በቪክቶሪያ ስትሪት ፍሌሚንግተን አዲስ ቤት ውስጥ

# አዳዲስ የማህበራዊ መኖሪያ ቤቶች በፍሌምንግተን



በአካባቢዎ ያሉ ያረጁ ከፍተኛ ፎቆች የአገልገሎት ጊዜያቸው እንዲያበቃ ለማድረግ ስንቃረብ፣ እነዚህ በቪክቶሪያ ስትሪት፣ ፍሌምንግተን ያሉ ቤቶች በሚያምር ሁኔታ የተነደፉ፣ ኃይል ቆጣቢ እና አሁን ካለው ሰፈር እና ማህበረሰብ ጋር ግንኙነቶችን ለማስቀጠል ምቹ ናቸው።

እነዚህ ቤቶች በ2023 መገባደጃ ላይ ይጠናቀቃሉ ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን በቅርቡም እርሶ እንዲያዩዋቸው ዝግጁ ይሆናሉ።



ምስል፦ በቪክቶሪያ ስትሪት ፍሌሚንግተን አዲስ ቤት ውስጥ

## የቪክቶሪያ ስትሪት ልማት

እነዚህ አዳዲስ ቤቶች የቪክቶሪያ ስትሪት አድራሻን አከባቢ፣ የትምህርት ቤቶችን አቅራቢያ፣ ሬይስኮርስ ሮድ የገበያ መንደርን እና አሁን ባለው የፍሌምንግተን ባለ ከፍተኛ ፎቅ መኖሪያ ቤቶች ጠርዝ ላይ ያለውን ስፍራ የሚቻላቸውን ያህል ይጠቀማሉ።

ተጨማሪ አዳዲስ ቤቶችን እና ክፍት ስፍራችን ጨምሮ በዚህ ቦታ ላይ ሌሎች የማስፋፊያ ማሻሻያዎች በእቅድ ደረጃ ላይ ናቸው።






## ኮምዩኒቲ ሃውሲንግ ቪክቶሪያ ሊምትድ (Community Housing Victoria Limtied)

እነዚህ ቤቶች የሚተዳደሩት በታላቅ ልምድ እና ለአገልግሎት ቁርጠኝነት ባላቸው ኮሙውኒቲ ሃውሲንግ ቪክቶሪያ ሊምትድ ነው። በቅርቡ የአገልግሎት ዘመናቸው ከሚያበቁት ፎቆች እንደሚዛወር ተከራይ፣ **የተከራይ መብቶችዎ ወይም በኪራይ ሁኔታዎ ላይ ምንም ለውጥ አይኖርም።**

# አዳዲስ ቤቶች በቪክቶሪያ ስትሪት፣ ፍሌምንግተን

እነዚህ ለዘላቂነት በሚያመች መልኩ የተነደፉ ባለ ኤሌክትሪክ ቤቶች አመቱን ሙሉ የሚመቹ እና ለማሞቅ እና ለማቀዝቀዝ ርካሽ ይሆናሉ። ሁሉም ነዋሪዎች በገበያ ውስጥ ምርጥ ተመኖችን እና 100% ታዳሽ ሃይልን ለማቅረብ ተካተው ከተዘረጉት የአካባቢ የሃይል አውታሮች ጋር ይገናኛሉ።

ሁሉም ቤቶች ጥሩ የተፈጥሮ ብርሃን እና አየር ማናፈሻ፣ ጥሩ መጠን ያላቸው የመጋዘን ቦታዎች እና ዘመናዊ መገልገያዎችን ከሰገነት ወይም ከጓሮዎች ጋር ይኖራቸዋል።

## ባህሪያት

**1፣ 2፣ 3** እና **4** መኝታ ቤቶች ያላቸው ቤቶች

**ብር** የመኖሪያ ቤት ንድፍ ደረጃ

**ከጋዝ-ነጻ የሆኑ** ቤቶች

**ተደራሽ** ማረፊያ

**5 ኮከብ**

አረንጓዴ ኮከብ ደረጃ

**7 ኮከብ**

ናተርስ መካከለኛ ደረጃ

## ይጎብኙ

በሚቀጥሉት ሳምንታት እነዚህ ቤቶች እርሶ እንዲያዩ ይዘጋጁልዎታል።

ስለ ባህሪያቸው እና ተስማሚነታቸው የበለጠ ለማወቅ በተዘጋጀው የጉብኝት መርሃ-ግብር እንዲቀላቀሉን ተጋብዘዋል።

የጉብኝቱ አካል መሆን ከፈለጉ እባክዎን ወደ **relocationsteam@homes.vic.gov.au** ኢሜይል ያድርጉ፣ ወይም በስልክ **1800 716 866** ይደውሉ።





በቪክቶሪያ ስትሪት፣ ፍሌምንግተን በወፍ በረር የተነሳ የአዳዲስ ቤቶች ፎቶ

## ወደ አዲስ ቤት መዛወር

ልዩ ፍላጎቶችዎን የሚያሟላ አዲስ ቤት እንዲያገኙ እና እርስዎን ከጎረቤት እና ከማህበረሰብ ጋር መገናኘት እንዲቀጥሉ ልንረዳዎ ዝግጁ ነን።

ከእነዚህ ቤቶች ውስጥ በአንዱ ላይ ፍላጎት ሊኖርዎት ይችላል ወይም ስለ መዛወር ሂደት ወይም ሌሎች አማራጮች ከአንድ ሰው ጋር መነጋገር ይፈልጉ ይሆናል።

በ **relocationsteam@homes.vic.gov.au** ኢሜል ይላኩልን ወይም በስልክ **1800 716 866** ይደውሉ ወይም በአካባቢዎ የሚገኘውን የቤቶች ቢሮ ያነጋግሩ።

የእርስዎን ፍላጎቶች፣ ተመራጭ ቦታዎች እና የማመልከቻውን ሂደት ለመወያየት የሚስማማዎትን ጊዜ እናዘጋጅልዎታለን።

የቤተሰብ አባላት ለመሳተፍ ይችላሉ እና የአስተርጓሚ ድጋፍን ማዘጋጀት እንችላለን።



## ተጨማሪ ይወቁ

ስለ ቪክቶሪያ ስትሪት፣ ፍሌምንግተን መልሶ ማልማት የበለጠ ለማወቅ እባክዎን ከታች ያለውን ድረ-ገጻችንን ይጎብኙ

ስካን ያድርጉኝ

homes.vic.gov.au/victoria-street-flemington

አዳዲስ ነገሮች እና ክንውኖች ሲኖሩ መረጃ እንዲደርስዎ ለመመዝገብ ኢሜይል ያድርጉ:-

**enquiries@homes.vic.gov.au**

የእኛን **@homesvic** የማህበራዊ መገናኛ ገጾች ይከተሉ

homes victoria

VICTORIA State Government | Families, Fairness and Housing

በቪክቶሪያ መንግስት የተፈቀደ እና የታተመ፣ 1 Treasury Place, Melbourne. © State of Victoria, ሆምስ ቪክቶሪያ፣ ጥቅምት 2023። በፊንስበሪ ግሪን (HV015623) የሚተዳደር ህትመት